# የተሻሻለዉ የ1995 ዓ.ም

## የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሕገ መንግሥት ማሻሻያ አዋጅ

ታህሳስ 9/1995 ዓ.ም

ጋ ም ቤ ላ

አዋጅ ቁጥር 27/1995

# በ1995 ዓ/ም የተሻሻለው የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ

በክልሉ ነዋሪ ሕዝብ በስፋትና በዝርዝር ተመክሮበት እስከ አሁን በሥራ ላይ የዋለውን ሕገ-መንግሥት አሁን በተጨባጭ እየታየ ባለው አጠቃላይ ሁኔታ የክልል መንግሥት አሰራርን የሚመለከቱ ክፍተቶችና ተጠያቂነትን በግልፅ በሚያሳይ መልኩ ማሻሻል ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ በሥራ ላይ ያለው የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 100 መሠረት ይህ የተሻሻለው የ1994 ዓ.ም የክልሉ ሕገ መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ ታውጇል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ አዋጅ የተሻሻለው የ1995 ዓ.ም የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 27/1995 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>በ1995 ዓ/ም የተሻሻለው የ1995 ዓ.ም ሕገ መንግሥት ስለመጽደቁ</u>

   በአዋጅ ቁጥር 2/1988 የፀደቀው የክልሉ ሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች ይዘትና አቀማመጥ በሰፊው ከታየ በኋላ በ1995 ዓ.ም ተሻሽሎ ተዘጋጅቶ የወጣው የጋምቤላ ሕዝቦች ክልላዊመንግሥት ሕገ መንግሥት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

3. <u>ስለ ነባር ሕጎች ተፈፃሚነት</u>

   በሥራ ላይ ያለ ማንኛውም ነባር ሕግ ከተሻሻለው ሕገ መንግሥት ጋር እስካልተቃረነ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

4. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

   ይህ አዋጅ የተሻሻለው ሕገ መንግሥት ከዛሬ ታህሳስ 9 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ጋምቤላ ታህሳስ 9 ቀን 1995 ዓ.ም

ኦኬሎ ኛጌሎ

የጋምቤላ ሕዝቦች ክልል ፕሬዚዳንት

# የተሻሻለዉ የ1995 ዓ/ም የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት

## መግቢያ

እኛ የጋምቤላ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሀገራችንና በክልላችን ተንሰራፍቶ የቆየዉን የጭቆና ሥርዓት ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችንን አፍኖ በተካሄዱ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ፖሊሲዎች በመከተሉ ስደተኝነትና ለኋላቀርነት ዳርጎን መቆየቱ በማያዳግም ሁኔታ መቀረፍ ያለበት መሆኑን በማመን የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን በነፃ ፍላጎታችን በክልላችን የሕግ የበላይነት ለማክበርና ለማስከበር ባለን ጽኑ እምነት ላይ በመመርኮዝ ክልላችንን በጋራ ለመገንባት የሚያስችለን የብሔረሰቦችን ሃይማኖቶች ጠቃሚ ባህሎችና ልምዶች ምንም ልዩነት ሳይደረግባቸዉ እንዲራመዱ ዓላማችን በመሆኑ፤

የክልላችን ሕዝቦች ለረጅም ዓመታት አብረዉና ተሳስረዉ የኖሩና ይህን አብሮ የመኖር ባህልና ልምድ በማጎልበት ለልማታችንና ለእድገታችን በጋራ በጠንካራ መሠረት ላይ በመቆም ወደ ተሻለ የእድገት ጉዞና እንድንመራ ፅኑ እምነት ያለን በመሆኑ፤

እኛ የአኝዋ፣ የኑዌር፣ የመዠንገር፣ የኦፓና የኮሞ ብሔረሰቦች ለተፋጠነ ኢኮኖሚ ዕድገት ለዘላቂ ሠላምና ዲሞክራሲ የምንሻዉ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን ሕገ መንግሥት መሠረት ያደረገና የክልላችንን ተጨባጭ ሁኔታዎች ያገናዘበ የክልላችን ሕገ መንግሥት ሊኖረን መሆኑን በሙሉ በመረዳት፤

እስከ አሁን በሥራ ላይ ያለዉን የ1988 ዓ.ም ሕገ መንግሥታችንን አሁን በተጨባጭ እየታየ ባለዉ ሀገራዊ ሁኔታና ክልላዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ግልጽ አሠራርን የሚከተል ለመረጠዉ ሕዝብ ተጠያቂ የሆነና ብቃት ያለዉ መንግሥታዊ አደረጃጀትን በሚያመላክት መልኩ አግባብ ያለዉ ጥልቅ እይታ ተደርጎበት ተሻሽሎ መዉጣት ያለበት መሆኑን በማመን፤

እነሆ ዛሬ ታህሳስ ፬ ቀን 1995 ዓ.ም በጋምቤላ ከተማ በተካሄደዉ የክልሉ ምክር ቤት ፲ኛ መደበኛ ጉባዔ የቀረበዉን የተሻሻለ የክልሉ ሕገ መንግሥት መክረንና በዝርዝር ተወያይተን በሙሉ ድምጽ አጽድቀናል።

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1

### የክልሉ መንግሥት ስያሜ

ይህ ሕገ መንግሥት የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ አወቃቀርን ይደነግጋል። በዚህም መሠረት የሚቋቋመው መንግሥት " የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት " በሚል ስም ይጠራል።

### አንቀጽ 2

### የጋምቤላ ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ክልል ወሰን

የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 1/8 በተደነገገው መሠረት የጋምቤላ ሕዝቦች ክልል ተብሎ የተጠቀሰው ነው። በዚህ መሠረት በምሥራቅ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል፣ በደቡብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ ከሱዳን ሪፐብሊክ በሰሜን ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት፤ በደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ከደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጋር የሚዋሰነው መልክዓ ምድር ነው።

### አንቀጽ 3

### ሰንደቅ ዓላማ

የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሰንደቅ ዓላማ ከላይ ቀይ፣ከመሐል ነጭና አረንጓዴ፣ ከታች ጥቁር ሆኖ በነጩ ቀለም መሐል ጥቁር ኮከብ ምልክት ያለው ነው። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

### አንቀጽ 4

### የክልሉ መንግሥት ዓርማ

የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ዓርማ በመሐሉ የበቆሎ እሸት፣ በስተቀኝ የተሰቀለ ባህላዊ ከበሮ፣ በስተግራ ዓሣ ያለበት ሆኖ ዙሪያው በጥብጣብ የተያዘ የዘንባባ ዝንጣፊዎችን የያዘ ነው። ዝርዝሩም በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 5

## የክልሉ ብሔራዊ መዝሙር

የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል የራሱ የሆነ ብሔራዊ መዝሙር ይኖረዋል። የክልሉ መዝሙር የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎችንና የክልሉን ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ አብሮ ለመኖር ያላቸውን እምነት እንዲሁም የወደፊት የጋራ ዕድላቸውን የሚያንፀባርቅ ሆኖ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 6

## የሥራ ቋንቋ

1. የክልሉ የሥራ ቋንቋ አማርኛ ይሆናል።

2. እንደየብሔረሰቡ ቋንቋው የተለያየ ይሁን እንጂ የክልሉ ቋንቋዎች ሁሉ በክልሉ ሕገ መንግሥት እኩል እውቅና ይኖራቸዋል።

3. የክልሉ ብሔር ብሔረሰቦች በራሳቸዉና በፈለጉት ቋንቋ የመማር መብት አላቸዉ

4. በክልሉ የሚገኙ ሕዝቦች በአማርኛ የመማር መብት አላቸዉ።

## አንቀጽ 7

## ርዕሰ ከተማ

የክልሉ ርዕሰ ከተማ ጋምቤላ ነዉ። [illegible] [illegible] ይደነገጋል።

## አንቀጽ 8

## የጾታ አገላለጽ

በዚህ ሕገ መንግሥት ዉስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገዉ የሴቷንም ጾታ ያካትታል።

## ምዕራፍ ሁለት

## የሕገ መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች

### አንቀጽ 9

### የሕዝቡ ሉዓላዊነት

1. የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል ሕዝብ የክልሉ ብሔራዊ መንግሥት የበላይነት ሥልጣን ባለቤት ናቸው፡፡

2. የሕዝቡ የበላይነት የሚገለፀው በሚመርጣቸው ተወካዮችና ራሱ በቀጥታ በሚያደርገው ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነው፡፡

### አንቀጽ 10

### የሕገ መንግሥቱ የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1. ይህ ሕገ መንግሥት የብሔራዊ ክልሉ የበላይ ሕግ ነው፡፡ ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ እንዲሁም የማንኛውም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ፣ የመንግሥት አካል፣ የፖለቲካ ድርጅትና ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ሕገ መንግሥቱን የማስከበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡

3. በዚህ ሕገ መንግሥት ከተደነገገው ውጭ በማንኛውም አኳኋን የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው፡፡

## አንቀጽ 11

## ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ በተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው።

2. የግለሰቦችና የሕዝቦች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸው።

## አንቀጽ 12

## የመንግሥትና ሐይማኖት መለያየት

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው።
2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም።
3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም።

## አንቀጽ 13

## የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

1. የክልሉ መንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት።

2. ሕዝቡ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ሊያነሳው ይችላል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

3. ማንኛውም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል በሕግ ተጠያቂ ይሆናል።

## ምዕራፍ ሦስት

## መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች

### አንቀጽ 14

### ተፈጻሚነትና አተረጓጎም

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ መንግሥት የሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካላት በዚህ ምዕራፍ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው።
2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ሰነዶች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማል

## ክፍል አንድ

## ሰብዓዊ መብቶች

### አንቀጽ 15

### የሕይወት፣ የአካል ደህንነትና ነፃነት መብት

ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና ነፃነት መብት አለው።

### አንቀጽ 16

### በሕይወት የመኖር መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው። ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም።

### አንቀጽ 17

### የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው።

## አንቀጽ 18
## የነፃነት መብት

1. በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ነፃነቱን አያጣም።
2. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም።

## አንቀጽ 19
## ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ኢ-ሰብዓዊ በሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም። ለማንኛውም ዓላማ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው።
3. ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛውም ሥራ እንዲሰራ ማድረግ የተከለከለ ነው።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት የሚሰራ ሐረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አይጨምርም።

ሀ/ ማንኛውም እስረኛ በእስር ባለበት ጊዜ በሕግ መሠረት እንዲሰራ የተወሰነውን ወይም በገደብ ከእስር ከተለቀቀበት ጊዜ የሚሰራውን ማንኛውንም ሥራ፣

ለ/ ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትክ የሚሰጠው አገልግሎት፣

ሐ/ የማህበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛውም አገልግሎት፣

መ/ በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ፣ በአካባቢው የሚፈፀመውን ማንኛውንም የኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት ሥራ፣

## አንቀጽ 20
## የተያዘ ሰው መብት

1. ወንጀል ፈጽሟል በመባል የተያዘ ሰው የቀረበበት ክስና ምክንያቱ በዝርዝርና ወዲያውኑ በሚገባው ቋንቋ እንዲነገረው መብት አለው።

2. የተያዘ ሰው ላለመናገር መብት አለው። የሚሰጠው ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል መረዳት በሚችለው ቋንቋ እንደተያዘ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጠው መብት አለው።

3. የተያዘ ሰው በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አለው። ሆኖም ይህ የጊዜ ገደብ ሰውየው ከተያዘበት ቦታ ወደ አቅራቢያው ፍርድ ቤት ለማምጣት አግባብ ባለው ሁኔታ የሚወሰደውን ጊዜ አይጨምርም። ወዲያውኑ ፍ/ቤት እንደቀረበም በተጠረጠረበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተገልጾ እንዲገለጽለት መብት አለው።

4. የያዘው አካል /ፖሊስ/ ወይም የሕግ አስከባሪ ወገኑ ገደቡ መሠረት ፍርድ ቤት በማቅረብ ካልቻሉ የተያዘበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነቱን እንዲያስከብርለት የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አለው። ሆኖም ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠይቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቀድ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የሕግ አስከባሪ ባለሥልጣናት ምርመራውን አጣርተው የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለውን መብት የሚያስከብር መሆን አለበት።

5. የተያዘ ሰው በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጥ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምን አይገደድም። በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።

6. የተያዘ ሰዉ በዋስ የመፈታት መብት አለዉ:: ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤቱ ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታት ጭምር በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል::

## አንቀጽ 21

## የተከሰሰ ሰዉ መብት

1. በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ ክስ ከቀረበበት በኋላ ተገቢ በሆነ ጊዜ ዉስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት በሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አለዉ:: የተከራካሪዉን የግል ሕይወት፣ የሕዝቡን የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል::

2. ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገረዉና ክሱን በጽሑፍ የማግኘት መብት አለዉ::

3. በፍርድ ሂደት ባለበት ጊዜ በተከሰሰበት ወንጀል እንዲናገርና ያለመናገር በምስክርነት እንዲቀርብም ያለመገደድ መብት አለዉ::

4. የተያዘ ሰዉ የቀረበበትን ማንኛዉም ማስረጃ የመመልከት የቀረበበትንም ምስክር የመጠየቅ ለመከላከል የሚያስችለዉን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የሚቀርብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበዉ እንዲሰሙለት የመጠየቅ መብት አለዉ::

5. በመረጠዉ የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣቱ ፍትሕ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አለዉ::

6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠዉ ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ሥልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለዉ::

7. የፍርድ ሂደት በማይገባዉ ቋንቋ በሚካሄድበት ጊዜ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምለት የመጠየቅ መብት አለዉ::

## አንቀጽ 22

## በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰዉ መብት

1. በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰዉ ሰብዓዊ ክብሩን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አለዉ።

2. ከትዳር ጓደኛዉ፣ ከቅርብ ዘመዶቹ ከሃይማኖት አባቶች ከአማካሪዎቹ፣ ከሐኪሞች ጋር የመገናኘትና እንዲጎበኙት ዕድል የማግኘት መብት አለዉ።

## አንቀጽ 23
## የወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ

1. ማንኛዉም ሰዉ የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈፃሚ ከነበረዉ የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛዉም ሰዉ ላይ አይወሰንበትም።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ( 1 ) ቢኖርም ድርጊቱ ከተፈፀመ በኋላ የወጣ ሕግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣዉ ሰዉ ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣዉ ሕግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

## አንቀጽ 24
## በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛዉም ሰዉ በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ዉሣኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም።

## አንቀጽ 25
## የክብርና የመልካም ስም መብት

1. ማንኛዉም ሰዉ በማንኛዉም ሥፍራ በሰብዓዊ ፍጡርነቱ እዉቅና የማግኘት መብት አለዉ።

2. ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩንና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው።

3. ማንኛውም ሰው የራሱን ሰብዕና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነፃ የማሳደግ መብት አለው።

## አንቀጽ 26
## የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው። በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው።

## አንቀጽ 27
## የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱና ሚስጢሩ የመከበር መብት አለው። ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት የመጠበቅ መብት ያጠቃልላል።

2. ማንኛውም ሰው በግል የሚፈጽማቸውና የሚቀበላቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም።

3. የመንግሥት ባለሥልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው። አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነትን፣ የሕዝብን ሰላም፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ የመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሰረቱ ዝርዝር ሕጎች መሠረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም።

## አንቀጽ 28

## የሐይማኖትና የእምነት ነፃነት

1. ማንኛዉም ሰዉ የማሰብ፣ የሕሊናና የሐይማኖት ነፃነት አለዉ። ይህ መብት ማንኛዉም ሰዉ የመረጠዉን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ የሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል።

2. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 122 ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰ እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸዉን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችላቸዉ የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማትን ለማቋቋም ይችላሉ።

3. ማንኛዉም ሰዉ የሚፈልገዉን እምነት ለመያዝ ያለዉን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም።

4. ወላጆችና ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸዉ መሠረት የሐይማኖታቸዉንና የሥነ ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸዉን የማሳደግ መብት አላቸዉ።

5. ሃይማኖትንና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለዉ የሕዝብን ደህንነት፣ ሰላም፣ ጤና፣ ትምህርት የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜጎችን መሠረታዊ መብቶች ነፃነቶችና መንግሥት ከሃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል።

## አንቀጽ 29

## በሰብአዊነት ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸዉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች በሰዉ ልጅ ላይ የተፈፀመዉ ወንጀሎች ተብለዉ የተወሰኑትን ወንጀሎች፣ የሰዉ ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመዉሰድ በአስገዳጅነት ሰዉን የመሰወር ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈፀሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ

አይቋረጥም:: በሕግ አውጭው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በምህረት ወይም በይቅርታ አይታለፉም::

## ክፍል ሁለት
## ዲሞክራሲያዊ መብቶች

### አንቀጽ 30
### የአመለካከት እና ሃሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት

1. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት መያዝ ይችላል::

2. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሃሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለው:: ይህ ነፃነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሃሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበል የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል::

3. የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የሥነ ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል:: የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል፤

   ሀ/ የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን፣

   ለ/ የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት እድልን::

4. ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሃሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል::

5. በመንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ

መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመሩ ይደረጋል።

6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሃሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰብም ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ሕጎች ብቻ ይሆናል። የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ሥርዓቶች በእነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ። የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በሕግ የሚከለከሉ ይሆናሉ።

7. ማንኛውም ዜጋ ከላይ ለተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦች ጥሶ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ ይሆናል።

## አንቀጽ 31

## የመሰብሰብ፣ ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው። ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሠላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሠላማዊ ሠልፍ ሠላምን፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥስ ለማስጠበቅ አግባብነት ያላቸው ሥርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ።

2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ሕጎች መሠረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም።

## አንቀጽ 32

## የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም አግባብ ያለውን ሕግ በመጣስ ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 33

## የመዘዋወር ነፃነትና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት መብት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 32 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በሕጋዊ መንገድ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ሰው በመረጠው የክልሉ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት፣ ሠርቶ የመኖር፣ ሀብትና ንብረት የማፍራት፣ የመሸጥ እንዲሁም በፈለገ ጊዜ ከክልሉ የመውጣት መብት አለው።

## አንቀጽ 34

## የመሥራት መብት

የክልሉን የሥራ ቋንቋ የሚያውቅ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም የክልሉ መንግሥታዊ ሥራዎች ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ የመሥራት መብት አለው።

## አንቀጽ 35

## የጋብቻ የግልና የቤተሰብ መብቶች

1. በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በሃይማኖት ወይም በሌሎች ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመሥረት መብት አላቸው። በጋብቻ አፈጻጸም፣ በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው። በፍቺ ጊዜ የልጆችን መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ የሕግ ድንጋጌዎች ይወጣሉ።

2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ብቻ ይመሰረታል።

3. ቤተሰብ የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው። ስለሆነም ከኅብረተሰቡና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው።

4. በሕግ በተለይ በሚዘረዘረው መሠረት በሃይማኖት፣ በባህልና በልማድ ሥርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል።

5. ይህ ሕገ መንግሥት የግልና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖቶች ወይም በባህሎች ሕጎች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 35
## የሴቶች መብት

1. ሴቶች ይህ ሕገ መንግሥት በአረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።

2. ሴቶች በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገው መሠረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው።

3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት ሲታዩ በመቆየታቸው ምክንያት የደረሰባቸውን የታሪክ ጠባሳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይኸው የታሪክ ጠባሳ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው። በዚህ ረገድ የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚዊ እንዲሁም በመንግሥትና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው።

4. ሴቶች ከጎጂ ልማድ ተፅዕኖ ለመላቀቅ ያላቸውን መብት መንግሥት ማስከበር አለበት። ሴቶችን የሚጨቁኑና በአካላቸው ወይም በአእምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች፣ ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው።

5. ሴቶች የቅጥር፣ የሥራ ዕድገት፣ የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው።

6. በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወይም በግል ድርጅት ተቀጥረው የሚሰሩ ሴቶች፣

ሀ/ የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው። የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሰራን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት፣ የሕፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል።

ለ/ የወሊድ ፈቃድ በሕግ በሚወሰነው መሠረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድ ሊጨምር ይችላል።

7. ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መረጃና አቅም የማግኘት መብት አላቸው።

8. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው። በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ የማስተላለፍ፣ የማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው። እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው።

9. ሴቶች በብሔራዊ ክልሉ የልማት ፖሊሲዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈጻጸም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ላይ ሃሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው።

## አንቀጽ 37
## የሕፃናት መብት

1. ማንኛውም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት፡፡

ሀ/ በሕይወት የመኖር፣

ለ/ ስምና ዜግነት የማግኘት፣

ሐ/ ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

መ/ ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርቱ፣ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎችን እንዲሰራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፤

ሠ/ በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈፀም ወይም ጭካኔና ኢሰብዓዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን።

2. ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ ከመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጭ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀዳሚነት መታሰብ አለበት።

3. ወጣት አጥፊዎች፣ በማረሚያ ወይም በማቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ በመንግሥት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች በመንግሥት ወይም የግል አሳዳጊዉታን ተቋሞች የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው።

4. ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ሕፃናት በጋብቻ ከተወለዱ ሕፃናት እኩል መብት አላቸው።

5. መንግሥት ለአሳዳጊዉታን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል። በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያጠናክርና የሚያስፋፋ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሠረቱ ያበረታታል።

## አንቀጽ 38
## ፍትህ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ውሳኔ ወይም ፍርድ፤

ሀ/ ማንኛዉም ማኅበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣

ለ/ ማንኛዉም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸዉን ሰዎች የሚወክል ማሕበረሰብ ወይም የቡድን ክስ የመመስረትና የማቅረብ መብት አለዉ።

## አንቀጽ 39
## የጋምቤላ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብቶች

የጋምቤላ ብሄር ብሄረሰቦችና ብሔራዊ ክልል ሕዝብ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለዉ መብቱ በማናቸዉም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነዉ። በዚህም መሠረት የብሔራዊ ክልሉ ሕዝብ፣

1 የራሱን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሱንና ታሪኩን የመንከባከብና የማበልጸግ እንዲሁም በቋንቋዉ የመጠቀም፣ ቋንቋዉን የማሳደግ፣ ባህሉን የመግለጽ የማዳበርና የማስፋፋት መብት አለዉ።

2 በራሱ መልክዓ ምድራዊ ክልል ዉስጥ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን፣ ራሱን በራሱ የማስተዳደርና እንዲሁም በፌዴራሉ መንግሥት ዉስጥ በሚኖት፣ እኩልም በሰለበት ተገቢና ፍትሃዊ በሆነ የዉክልና አግባብ ዉሳኔ ሰጪ ተሳትፎ የማድረግ መብት አለዉ።

3 የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል ሕዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራል መንግሥቱ አስተዳደሮች ዉስጥ ሚዛናዊ ዉክልና የማግኘት መብት አለዉ።

4 በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተጠቀሱት መብቶች ታግዶ ተረግጦ ወይም ተሸራርፎ ብሎ በመገበቱና እንደዚሁም በአንድነት አብሮ ሆኖ ሊያስተካክላቸዉ ባልቻለበት ጊዜ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 በተደነገገዉ መሠረት የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ድረስ ተግባራዊ ያደርጋል።

5. የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በሥራ ላይ የሚውለው፡

ሀ/ የመገንጠሉ ጥያቄ በክልሉ ምክር ቤቱ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፤

ለ/ የክልሉ ምክር ቤት የመገንጠል ውሣኔ በደረሰበት በሶስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ የፌዴራሉ መንግሥት ሕዝበ ውሣኔ ሲያደራጅ፤

ሐ/ የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝበ ውሣኔ በአብላጫው ድምጽ ሲደገፍ፤

መ/ የፌዴራሉ መንግሥት መገንጠሉን ለመረጠው ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ምክር ቤት ሥልጣኑን ሲያስረክብና፤

ሠ/ በሕግ በሚወሰነው መሠረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው።

6. በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ማለት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ባህሪያት የሚያሳይ ማህበረሰብ ነው። ሰፊ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፤ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው የጋራ ወይም የተያያዘ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑና የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው።

## አንቀጽ 40
## የንብረት መብት

1. በክልሉ ውስጥና ውጭ የሚኖር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል። ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረት የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል።

2. ለዚህ አንቀጽ አላማ የግል ንብረት ማለት በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጭ የሚኖር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም ሕጋዊ ሰውነት በሕግ የተሰጣቸው አገር

አቅፎ ወይም ከሌላ ሰው ማኅበራት ወይም አንድነት ባላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለይ በጋራ የንብረት ባለቤቶች እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማኅበረሰቦች፣ በጉልበታቸው፣ በፈጠራ ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው የአፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ባይኖረው ዋጋ ያለው ዉጤት ነው።

የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የክልሉ የሕዝብ የጋራ ንብረት ነው።

4. የክልሉ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸው የተከበረ ነው። አፈጻጸሙ በሕግ ይወሰናል።

5. በክልሉ የሚገኙ አርብቶ አደሮች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት አላቸው። አፈጻጸሙ በሕግ ይወሰናል።

6. የመሬት ባለቤትነት የሕዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በሕግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

7. በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጭ የሚኖር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ የሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው። ይህም መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ደግሞ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብቶችን ያካትታል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

8. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል።

## አንቀጽ 41

## የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶች

1. የክልሉ ነዋሪ የሆነ ወይም በክልሉ ዉስጥ ለመኖር የሚፈልግ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በክልሉ ዉስጥ በማንኛዉም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያዉ የመረጠዉን ሥራ የመሥራት መብት አለዉ።

2. ማንኛዉም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያዉን፣ ሥራዉንና ሙያዉን የመምረጥ መብት አለዉ።

3. የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄዱ ማህበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸዉ።

4. የክልሉ መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝቡ ለማቅረብ በየጊዜዉ እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል።

5. የክልሉ መንግሥት የአካልና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕጻናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደዉ ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል።

6. የክልሉ መንግሥት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፤ እንዲሁም በሚያካሂደ የሥራ ዘርፍ ዉስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል፤ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል።

7. የክልሉ መንግሥት የክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት ዕድላቸዉ እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

8. ገበሬዎች እና አርብቶ - አደሮች በሚያገኙዉ እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸዉንና ለብሔራዊ ሀብት ካደረጉት የምርት አስተዋጽኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ዉጤታቸዉ የማግኘት መብት አላቸዉ። የክልሉ መንግሥት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲዎችን በሚነድፍበት ጊዜ በዚህ ዓላማ መመራት አለበት።

9. የክልል መንግሥት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለሥነ ጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## አንቀጽ 42
## የሠራተኞች መብት

1. የፋብሪካና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ከዚህም ሌሎች የገጠር ሠራተኞች ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች፡-

ሀ/ የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማኅበር የመደራጀት መብት አላቸው። ይህ መብት የሠራተኛ ማኅበራትንና ሌሎች ማኅበራትን የማደራጀት ከአሠሪዎችና ጥቅሞቻቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብቶች ያካትታል።

ለ/ ከዚህ በላይ ንዑስ አንቀጽ ሥር የተመለከቱት የሠራተኞች ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታ ለማሰማት መብት አላቸው።

ሐ/ ከፍ ብሎ በፊደል ተራ ቁጥሮች ሀ እና ለ መሠረት እዉቅና ዋስትና መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወሰናሉ።

መ/ ሴት ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው።

2. ሠራተኞች በሕግ የተወሰነ የሥራ ሰዓት ዕረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀናት ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው።

3. እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እዉቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት

የሠራተኛ ማህበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ፡፡

## አንቀጽ 43
## የልማት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተከበረ ነው፡፡

2. የክልሉ ነዋሪዎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማህበረሰብ በሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

3. የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የክልሉን ነዋሪዎች እድገትና መሠረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 44
## የአካባቢ ደህንነት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች ንፁህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው፡

2. የክልሉ መንግሥት በሚያካሂዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዛወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የክልሉ መንግሥት አወቃቀር

### አንቀጽ 45

### የክልሉ አስተዳደር እርከኖች

1. የክልሉ መንግሥት በክልል፣ በብሔረሰብ ዞን፣ በአስተዳደራዊ ወረዳዎችና በቀበሌዎች የተዋቀረ ነው። ይሁን እንጂ የክልሉ ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የአስተዳደር እርከኖች ሊያዋቅርና ሥልጣናቸውን በሕግ ሊወስን ይችላል።

2. በክልሉ ውስጥ የሚቋቋሙት የአስተዳደር እርከኖች በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ ማንነትና ፈቃድ ላይ በመመሥረት ይሆናል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ከተሞች ልማታቸውን የሚያፋጥን የራሳቸው አስተዳደር ይኖራቸዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

### አንቀጽ 46

### የክልሉ መንግሥት አባላት

1. የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መሥራች አባላት የሚከተሉት ብሔር ብሔረሰቦች ናቸው።

    1. የአኙዋ ብሔረሰብ
    2. የኑዌር ብሔረሰብ
    3. የመዠንገር ብሔረሰብ
    4. የኦፖ ብሔረሰብ
    5. የኮሞ ብሔረሰብ

2. የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል አባላት እኩል መብትና ሥልጣን አላቸው::

3. በእያንዳንዱ የብሔረሰብ ዞን በራሱ አስተዳደር ዉስጥ የሚገኙ ሌሎች አናሳ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የየራሳቸዉን ቀበሌዎች በራስ የማስተዳደር መብት ይጠበቃል፤ በክልሉና በዞን በውክልና የመሳተፍ መብትም ይጨምራል::

## አንቀጽ 47

## የአስተዳደር እርከኖች የአከላለል ለዉጦች

1. የአስተዳደር እርከኖች ወሰን በሚመለከት ጥያቄ የተነሣ እንደሆነ ጉዳዩ በሚመለከታቸው የአስተዳደር እርከኖች በስምምነት ይፈጸማል:: የሚመለከታቸዉ አካላት መስማማት ካልቻሉ ጉዳዩ የሚመለከተዉ የብሔረሰብ ምክር ቤት በውሣኔ ለክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ያቀርባል፣ የክልሉ ምክር ቤት የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ይወስናል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ 1 መሠረት የቀረበዉ ጉዳይ ከ3 ወር ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ በክልሉ ምክር ቤት የመጨረሻ ዉሣኔ ይሰጥበታል::

## ምዕራፍ ስምንት

## የክልሉ መንግሥት ሥልጣን አወቃቀር እና ክፍፍል

## አንቀጽ 48

## የክልሉ መንግሥት የሥልጣን አካላት

1. የክልሉ መንግሥት ሕግ አዉጪ አካል የክልሉ ምክር ቤት ሲሆን የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ተጠሪነቱ ለመረጠዉ ሕዝብ ነዉ::

2. የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈፃሚ አካል የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነዉ::

3. የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።

## አንቀጽ 49

## የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ውስጥ በውሉ ተለይተው ለፌዴራሉ መንግሥት ወይም ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሉ በጋራ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውጭ ያለ ማናቸውም ሥልጣንና ተግባር የክልሉ መንግሥት ሥልጣንና ተግባር ይሆናል።

2. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ክልላዊ መንግሥቱ፦

2.1 የክልሉ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፤

2.2 የክልሉ ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎችን ያወጣል፣ ያስፈጽማል፤

2.3 የፌዴራሉ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሠረት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል፤

2.4 ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያቋቁማል፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትንና ይህንን ሕገ መንግሥት ይጠብቃል፣ ይከላከላል፤

2.5 የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ሕግ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፤ ይህንን በሚያስፈጽምበት ጊዜ የሠራተኛውን የትምህርት፣ የሥልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

2.6 የክልሉን የፖሊስ ኃይል ያደራጃል፣ ይመራል፣ የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ይጠብቃል፤

2.7 የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 29 ድንጋጌዎች እንዲጠበቁ ሆነዉ በሕግ መሠረት ምህረት ያደርጋል።

2.8 ለክልሉ በተወሰነዉ የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶችን ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ የክልሉን በጀት ያወጣል፤

2.9 በክልሉ መስተዳድሩና በድርጅቶቹ ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፤

2.10 የመሬት መጠቀሚያ ክፍያን ይወስናል፤

2.11 የእርሻ ሥራ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፤

2.12 በክልሉ ዉስጥ በግል ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚያገኙ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፣ በክልሉ መስተዳድሩ ባለቤትነት ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላል፤

2.13 በክልሉ መስተዳድሩ ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ፣ የሥራ ግብርና የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክሶችን ይጥላል፣ ይሰበስባል፤

2.14 ከፌደራሉ መንግሥት ጋር፦

ሀ/ በጋራ ከሚያቋቁሟቸዉ የልማት ድርጅቶች የሚገኘዉን የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክሶችን በሕግ መሠረት ይከፍላል፤

ለ/ ከድርጅቶች የንግድ ትርፍና ከባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክሶችን በሕግ መሠረት ይከፈላል፤

ሐ/ ከከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና ከማናቸዉም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች የሚገኘዉን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በሕግ መሠረት ይከፈላል፤

2.15 በክልሉ መስተዳድሩ አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚገኙ ክፍያዎችን ይወስናል ይሰበስባል፤

2.16 ከደን የሚገኘዉ የሮያሊቲ ክፍያ ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

2.17 በክልሉ ውስጥ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ በሥራ ላይ ያውላል።

## ምዕራፍ ስድስት

## ስለ ክልሉ ምክር ቤት

### አንቀጽ 50

### ስለ ክልሉ ምክር ቤት አባላት

1. የክልሉ ምክር ቤት አባላት ነፃ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በሚስጥር በሚሰጥበት ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ።

2. የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሚወዳደሩት ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ። የተለየ ውክልና እንደሚያስፈልጋቸው የታመነባቸው አናሳ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችም በምርጫ ምክር ቤቱ ውስጥ ይወከላሉ። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

3. የምክር ቤቱ አባላት የመላው የክልሉ ሕዝብ ተወካዮች ናቸው። ተገዥነታቸውም፦

   ሀ/ ለሕገ መንግሥቱ
   ለ/ ለመረጣቸው ሕዝብ
   ሐ/ ለራሳቸው ሕሊና ብቻ ይሆናል።

4. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምጽ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፣ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም።

5. ማንኛውም የክልል ምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፤ በወንጀል አይከሰስም።

6. ማንኛውም የምክር ቤት አባል የመረጠዉን ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በሕግ መሠረት ከምክር ቤት አባልነቱ ይወገዳል

7. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ድንጋጌ እንደአግባብነቱ በየደረጃዉ በሚገኙ ምክር ቤቶች ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡

## አንቀጽ 51
## የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የክልል ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የክልሉ ሕግ አዉጭ አካል ነዉ፡፡

2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በክልላዊ ክልሉ የዉስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ነዉ፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ሥር የሰፈረዉ ሕጋዊ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በተለይ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

   3.1 በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የፌዴሬሽን ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎችን የማይፃረሩ ልዩ ልዩ ሕጎችን ያወጣል፡፡

   3.2 የሕዝቡን ብዛት፣ የክልሉን ስፋትና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ግምት ዉስጥ በማስገባት በክልሉ ዉስጥ ተጨማሪ የአስተዳደር እርከኖችን ወይም የራስ በራስ አስተዳደራዊ አካባቢዎችን ያቋቁማል፡፡

   3.3 የክልሉ ብሔረሰቦችን በመወከል በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚሳተፉትን በቀጥታ በሕዝብ ባልተመረጡበት ጊዜ ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መርጦ ይልካል፡፡

3.4 የፌዴራሉ መንግሥት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ከአጎራባች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጋር የሚደረጉ ስምምነቶችን ያፀድቃል።

3.5 የራሱን አፈ ጉባኤ ይመርጣል፤ ለምክር ቤቱ ሥራ የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ይሰይማል።

3.6 ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ርዕሰ መስተዳድሩን በምርጫ ይሰይማል፤ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ሹመት ያፀድቃል።

3.7 በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት፣ ም/ፕሬዚዳንት፣ ዋና ኦዲተሩንና ምክትል ዋና ኦዲተሩን ይሾማል።

3.8 የክልሉን ጠቅላይ፣ ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ያቋቁማል፤ ዳኞችን ይሾማል።

3.9 የኦዲትና ሌሎች የቁጥጥር አካላትን ያቋቁማል።

3.10 በሕጉ መሠረት ምክረት ያደርጋል፤ የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፤ የፀጥታና የፖሊስ ኃይሉን ያቋቁማል።

3.11 የክልሉን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራሞች ያፀድቃል።

3.12 የክልሉን የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ሕጎችን ያወጣል፤ የክልሉን በጀት መርምሮ ያፀድቃል።

3.13 ለማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋት፣ ለኢኮኖሚያዊ ልማት መፋጠንና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን ያቋቁማል።

3.14 ለክልሉ መንግሥት በተከለለው የገቢ ምንጭ በክልሉ ውስጥ ግብርና ታክስ ይጥላል።

3.15 የክልሉ መስተዳድሩን የሠራተኞች አስተዳደር የሥራ ሁኔታዎችን በተመለከተ ሕግ ያወጣል፤

3.16 በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2/ገ/ ሥር ለክልሉ መንግሥት በተሰጠዉ ሥልጣን መሠረት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጣል፤

3.17 የሀገሪቱንና የክልሉን ሕገ መንግሥታት አዋጆችንና ሌሎች ሕጎችን በክልሉ ዉስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝርዝር የማስፈጸሚያ ደንቦች ያወጣል፤

3.18 የክልሉን ርዕሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግሥት ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፤

3.19 ለብሔረሰብ ዞኖችና ለአስተዳደራዊ አርከኖች የሕዝብ ብዛትን ዋና መመዘኛ ባደረገ ቀመር በጀት ይመድባል።

## አንቀጽ 52
## የፖለቲካ ሥልጣን

1. በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ያደራጃል፤ ወይም ያደራጃሉ፤ ይመራል ወይም ይመራሉ፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደአግባብነቱ ለብሔረሰብ ዞን፣ ለብሔረሰብ ልዩ ወረዳ፣ ለወረዳ እና ለቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ተፈጻሚ ይሆናል።

## አንቀጽ 53
## ስለ ክልሉ ምክር ቤት ጽ/ቤት

1. የክልሉ ምክር ቤት የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል።
2. የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 54
## ስለ ምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. አብላጫ መቀመጫ ያገኙት የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት የክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 3/5 መሠረት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየም ሆኖ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነው።

2. አፈ ጉባኤው የሥራ ዘመን የክልሉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

3. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ለብሔረሰብ ዞን፣ ለብሔረሰብ ልዩ ወረዳ፣ ለወረዳና ለቀበሌ ምክር ቤቶች አፈ ጉባኤዎች ያገለግላሉ።

## አንቀጽ 55
## የአፈ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት የጽሕፈት ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል።
ይኖሩታል።

1. የምክር ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ይጠራል፣ ይመራል፣

2. ምክር ቤቱን በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፣

3. የምክር ቤቱን ጽ/ቤት ያደራጃል፣ ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣

4. ምክር ቤቱ በአባላቱ ላይ እንዲወሰድ የወሰናቸውን የዲሲፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል፣

5. የምክር ቤቱን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያስተባብራል፣

፲. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡

## አንቀጽ 56

## የምክትሉ አፈ ጉባኤዉ ሥልጣንና ተግባር

ምክትሉ አፈ ጉባኤዉ ተጠሪነቱ ለአፈ ጉባኤና ለክልሉ ምክር ቤት ነው።

1. በአፈ ጉባኤዉ ተለይተዉ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣
2. አፈ ጉባኤዉ በማይኖርበት ወይም ሥራዉን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

## አንቀጽ 57

## የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የክልሉ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት ዉስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባዉ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

   የምክር ቤቱ ዉሳኔ በስብሰባ ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል።

3. የክልሉ ምክር ቤት አባላት የሚመረጡ ለአምስት ዓመታት ነዉ። የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞዉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በ15 ቀናት ጊዜ ዉስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራዉን ይጀምራል።
4. ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ ጉባኤዉ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ወይም ምክር ቤቱ አባላት መካከል ከአንድ ሶስተኛዉ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ ጉባኤዉ የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

5. የክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል፤ ሆኖም ስብሰባዉ በዝግ እንዲካሄድ በምክር ቤቱ አባላት ወይም በክልሉ አስፈጻሚ አካል ከተጠየቀና ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄዉን ከደገፉት ምክር ቤቱ ዝግ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

## አንቀጽ 58

## የምክር ቤቱ ዉሳኔዎችና ዉስጣዊ የአሰራር ሥነ ሥርዓቶች

1. በዚህ ሕገ መንግሥት ዉስጥ ተገልጾ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸዉም ዉሳኔዎች የሚተላለፉት በምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምጽ ነዉ።

2. ምክር ቤቱ ዉስጣዊ አሰራሩንና የሕግ አወጣጡን ሂደት አስመልክቶ ዝርዝር ደንቦችን ሊያወጣና በሥራ ላይ ሊያዉል ይችላል።

# ምዕራፍ ሰባት

# የሕግ አስፈጻሚ አካል

## አንቀጽ 59

## የአስፈጻሚነት ሥልጣን

1. የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ሥልጣን የተሰጠዉ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነዉ።

2. ርዕሰ መስተዳድሩና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነታቸዉ ለክልሉ ምክር ቤት ነዉ።

3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ተግባራቸዉ በጋራ ስለሚሰጡት ዉሳኔ ስለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸዉ።

## አንቀጽ 60

## የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ፣ የአስፈጻሚ ቢሮዎች ኃላፊዎችና በሕግ በሚወሰነው መሠረት ሌሎች አባላት የሚገኙበት አካል ነው።

2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ ርዕሰ መስተዳድሩ ነው።

3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ነው።

4. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወስነው ውሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ተጠሪ ይሆናል።

## አንቀጽ 61

## የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ ሕግ የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በክልሉ ምክር ቤትና በፌዴራሉ መንግሥት የወጡ ሕጎችና የተላለፉ ውሳኔዎች በክልሉ ውስጥ በሥራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል፤ መመሪያዎችን ይሰጣል፤

2. የክልሉ መስተዳድሩ አስፈጻሚ አካላት የሥራቸው ተግባራት አደረጃጀት ይወስናል፤ ሥራቸውን ያስተባብራል፤ ይመራል፤

3. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 3.2 ድንጋጌዎች ሥር ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የሚቀርቡ የሽግሽግ ጥያቄዎችን አጣርቶ ይወስናል፤

4. የክልሉን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

5. የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣ የሕግ ረቂቆችን ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፣ የተወሰኑትንም ያስፈጽማል፡፡

6. በክልሉ ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፡፡

7. የክልሉ ምክር ቤት በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችንና መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

8. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፣ በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገው የጊዜ ወሰን ውስጥ የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፡፡

9. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 3.16 መሠረት ለክልሉ ምክር ቤት አስተድደር የተሰጠዉ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ ሊሰበሰብ ባልቻለበት ሁኔታ የጤና ችግርና ድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋ በክልሉ ውስጥ በሚደርስበት ጊዜ አስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አዉጥቶ በሥራ ላይ ያውላል፡፡

10. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 62

## የርዕሰ መስተዳድሩ አሰያየምና የሥራ ዘመን

1. ርዕሰ መስተዳድሩ በክልሉ ምክር ቤት ውስጥ አብላጫ መቀመጫ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል፡፡

2. በዚህ ሕገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የርዕሰ መስተዳድሩ የሥራ ዘመን የክልሉ ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ነው፡፡

3. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድርነት ምርጫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ከፀደቀ በኋላ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የጋራ ስብሰባዉ በተሰየመበት ጊዜ በስብሰባዉ ፊት ለሕገ-መንግሥቱና ለክልሉ ሕዝቦች ያለዉን ታማኝነት በሚገልጽ ቃላት ይገልጻል፡፡

እኔ ____________ በሃሬዉ ስለት የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል ርዕሰ መስተዳድር በመሆን ሥራዬን ስጀምር የተጣለብኝን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመፈጸም ቃል እገባለሁ።»

## አንቀጽ 63

## የርዕሰ መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ርዕሰ መስተዳድሩ የክልሉ መስተዳድሩ ሥራ መሪ፣ የመስተዳድር ምክር ቤቱ ሰብሳቢና የክልሉ ፕሬዚዳንት ነዉ።

2. ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ነዉ።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረዉ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ መስተዳድሩ፣

ሀ/ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይወክላል፤

ለ/ የክልሉ መንግሥት ሕግ አዉጭና ሕግ አስፈፃሚ ክፍሎች በየበኩላቸዉ መክረዉ ያፀደቋቸዉን አዋጆችና ደንቦች በጋምቤላ ነጋሪት ጋዜጣ ይታወጁ ዘንድ በአሥራ አምስት ቀናት ዉስጥ ፈርሞ ይልካል፣ በአሥራ አምስት ቀናት ዉስጥ ካልፈረመ ሕጉ በሥራ ላይ ይዉላል፤

ሐ/ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣቸዉን ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ዉሳኔዎች ተፈፃሚነት ይከታተላል፤

መ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትን፣ ምክትል ፕሬዚዳንትን፣ የክልሉን ዋና ኦዲተርና ምክትል ኦዲተር መርጦ ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስሾማል፤

ሠ/ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩን ጨምሮ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት የሚሆኑ የቢሮ ኃላፊዎችን ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል። ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የክልሉ ምክር ቤት አባል መሆን አለበት።

ረ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ ቁጥሮች መ እና ሠ ሥር የሰፈረው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የክልሉ ምክር ቤት ሲሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜና ሁኔታ ከምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ በመሳስ ያሉትን ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን የሥራ ኃላፊዎች በጊዜያዊነት መድቦ ያሠራል። የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትንና ምክትል ፕሬዚዳንቱን በጊዜያዊነት የሚመደበ- ከሳሾች መሾሙ ያፀናል፤

ሰ/ ከክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ዉጭ የሆኑ የቢሮ ኃላፊዎች፣ በክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ያሾማል፤ ምክትል የቢሮ ኃላፊዎች፣ ኮሚሽነሮችና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች መርጦ ይሾማል፤

ሸ/ የክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅና ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር የተቋቋሙት ክልል አቀፍ የሆኑትና የፖሊሲ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ቀ/ በክልሉ የሚገኙትን የቢሮዎች አስተዳደር አገልግሎቶች ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

በ/ የዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉን ምክር ቤት መሥራቾች ዓ/ኢ ይጠራል፤

ተ/ ለክልሉ ምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፤

ቸ/ በክልሉ ምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 64

## የምክትል ርዕሰ መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር

1. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ሹመቱ የሚፀድቅ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ/ በርዕሰ መስተዳድሩና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

ለ/ ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

2. ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነው።

## አንቀጽ 65

## የርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት

1. ርዕሰ መስተዳድሩ በዚህ ሕገ መንግሥት የተሰጡትን ኃላፊነት ለመወጣት ያስችለው ዘንድ የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል።

2. የርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ጽ/ቤት በመሆን ጭምር ያገለግላል።

3. የጽ/ቤቱ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 66

## ስለክልሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ተቋማት መቋቋም

1. የክልሉን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ የልማት ተግባራት ሥራዎችን የሚያከናውኑ፣ የሚያስተባብሩና የሚመሩ ልዩ ልዩ ቢሮዎች፣ ኮሚሽኖች፣ ጽ/ቤቶችና ሌሎች ተቋማት እንደአስፈላጊነታቸው ይቋቋማሉ።

2. የቢሮዎች፣ የኮሚሽኖች፣ ጽ/ቤቶችና ሌሎች ከፍተኛ ተቋማት ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ለመስተዳድር ምክር ቤቱ ይሆናል፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ ቢሮዎች፣ ኮሚሽኖች፣ ጽ/ቤቶችና ሌሎች ተቋማት ተጠሪነት ከነዋቋማቸው አላማና ከሚያከናውኑት ተልዕኮ ጋር አግባብነት ላላቸው የክልሉ መንግሥት የበላይ አስፈፃሚ መምሪያ ቤቶች ይሆናል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

# ምዕራፍ ስምንት

## ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና የዳኝነት ሥልጣን

### አንቀጽ 67

### ስለ ነፃ ዳኝነት አካል መቋቋም

1. የክልሉ ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል፡
2. የዳኝነትን ሥልጣን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጠዉ ተቋም ዉጪ የሚያደርግና በሕግ የተደነገገዉን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም።

### አንቀጽ 67

### ስለ ባህላዊና ሃይማኖታዊ የዳኝነት አካላት

በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 5 ሥር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ሕገ መንግሥት ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እዉቅና አግኝተዉ ሲሰሩባቸዉ የነበሩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካላት በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት እዉቅና አግኝተዉ ይደራጃሉ።

### አንቀጽ 68

### የዳኝነት ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነዉ ።
2. በየትኛዉም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸዉም የመንግሥት አካል፣ ባለሥልጣን ወይም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነዉ።
3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸዉን በሙሉ ነፃነት ያከናዉናሉ። ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።
4. ማንኛዉም ዳኛ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በሕግ የተወሰነዉ የጡረታ መዉጫ እድሜዉ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ዉጭ ከዳኝነት ሥራዉ አይነሳም።

ሀ/ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የዲሲፕሊን ሕግ መሠረት ጥፋት ፈጽሟል ወይም ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን ወይም፤

ለ/ በሕመም ምክንያት ዳኛው ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስንና፤

ሐ/ የጉባኤው ውሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍና ሲፀድቅ።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የሰፈሩት ድንጋጌዎች አፈጻጸም ዝርዝር በሕግ ይወሰናል።

6. የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም።

## አንቀጽ 69

## የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ሥልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት አካል በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ይደራጃል። የወረዳ ፍርድ ቤት የክልሉ ዝቅተኛና የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል ነው።

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣

ሀ/ ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛውና የመጨረሻው የዳኝነት ሥልጣን፤

ለ/ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣንና፤

ሐ/ ማናቸውም ክልላዊ ፍርድ ቤት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

3. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካለው ክልላዊ ሥልጣን በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሆን ይዳኛል።

4. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የሚቀርብለት ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰናል፡፡

5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት የሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የሚቀርብለት ይግባኝ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ ይወሰናል፡፡

6. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት አካላቱን የሚያስተዳድርበትን በጀት በማርቀቅ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፣ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል።

7. የክልሉ ፍርድ ቤቶች በዉክልና የሚፈፅሙትን ፌደራላዊ የዳኝነት ተግባር ለማከናወን የሚያወጡትን የገንዘብ ወጪ በተመለከተ ከፌደራል መንግሥት ማካካሻ እንዲሰጣቸዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ 70
## ስለዳኞች አሿሿም

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እና የወረዳ ፍርድ ቤቶች ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡

3. የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በእጩዎቹ ላይ ያለዉን አስተያየት መጠየቅና የተሰጠዉን አስተያየት ከራሱ መግለጫ ጋር ለክልሉ ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም የፌደራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተጠየቀዉን አስተያየት በሦስት ወራት ጊዜ ዉስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት የእጩዎቹን ሹመት ተቀብሎ ያጸድቃል፡፡

## አንቀጽ 71

## ስለ ክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ መቋቋም

1. በክልሉ ውስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምፅ የሚወከሉበት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይቋቋማል።

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ጉባኤውን በሰብሳቢነት ይመራል።

3. የጉባኤውን አባላት ዝርዝር፣ ስብጥር ፣ ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 72

## ሕገ መንግሥትን ስለመተርጎም

1. በክልሉ ውስጥ የሕገ መንግሥታዊ ክርክር ጉዳይ ወይም የትርጉም ጥያቄ ሲነሣ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ከእያንዳንዱ ብሔረሰብ ምክር ቤቶች በእኩልና በቁጥር ጭምር ተወጣጥቶ በወከልና የሚሰየም የሕገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

2. ኮሚሲዮኑ የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሚያቀርብለት ሕገ መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ መክሮ በስልሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ መሠረት የሚቋቋመው ኮሚሲዮን የአገልግሎት ዘመን አባላቱ የተወከሉባቸው የወረዳ ምክር ቤቶች የሥራ ዘመን ሲሆን መንግሥታዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ይሰበሰባል።

4. ኮሚሲዮኑ የራሱን ሰብሳቢና ፀሐፊ ከአባላቱ መካከል መርጦ ሥራውን የሚያከናውን ሲሆን ለሥራው የሚያስፈልገውን የጽሕፈት ቤት አገልግሎትና የፋይናንስ ድጋፍ ከክልሉ ምክር ቤት ያገኛል።

## አንቀጽ 73

## የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

1. የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል፡፡

2. የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አሥራ አንድ አባላት የሚኖሩት ሲሆን እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

   ሀ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሰብሳቢ፣

   ለ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ምክትል ሰብሳቢ፣

   ሐ/ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የሚሰየሙና በሙያ ብቃታቸውና በሥነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የሕግ ባለሙያዎች፣

   መ/ በአፈ ጉባኤው አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየሙ ሶስት ተወካዮች ፡፡

## አንቀጽ 74
## የአጣሪ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

1. የክልሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይህንን ሕገ መንግሥት መሠረት አድርገው ከክልሉ የሚመነጩ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ በሚያደርገው ማጣራት መሠረትም የክልሉን ሕገ መንግሥት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጉዳዩ ላይ የራሱን የውሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለሕገ መንግሥት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ያቀርባል፡፡

2. አጣሪ ጉባኤው በክልሉ መንግሥት አካላት የሚወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ በማናቸውም ሁኔታ ሲነሳና ጉዳዩ በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዮች አማካኝነት ሲቀርብለት ከመረመረና ካጣራ በኋላ የመጨረሻ ውሳኔ ለኮሚሲዮኑ ያቀርባል፡፡

3. በፍርድ ቤቶች ዘንድ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ ጉባኤው፤

   ሀ/ የክልሉን ሕገ መንግሥት መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ይመልሳል፡፡ ሆኖም ባለ

ጉባኤዉ ዉሳኔ ቅር የተሰኘ ማናቸዉም ባለጉዳይ ይህንኑ ቅሬታዉን በጽሑፍ አዘጋጅቶ ለኮሚሽኑ በደንባቡ ማቅረብ ይችላል::

ለ/ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠዉን የሕገ መንግሥታዊ ትርጉም አስናድቶ ለኮሚሽኑ ለመጨረሻ ዉሳኔ ያቀርባል::

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ስለ የብሔረሰብ አስተዳደሮች አደረጃጀትና ሥልጣን

### አንቀጽ 75

### የብሔረሰብ አስተዳደሮች አደረጃጀት

1. በብሔረሰብ አስተዳደሮች ዉስጥ የእንቅስቃሴ፣ኅብረትና የመስተጋብር ትስስሮች በሰፈሩባቸዉ አካባቢዎች በዚህ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ሥር በተደነገገዉ መሠረት የብሔረሰብ አስተዳደር ተቋቁሟል።

2. እያንዳንዱ ብሔረሰብ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል።

ሀ/ የብሔረሰብ ምክር ቤት

ለ/ የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት

ሐ/ የብሔረሰብ አስተዳደር የዳኝነት አካል

### አንቀጽ 76

### የብሔረሰብ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. እያንዳንዱ የብሔረሰብ ምክር ቤት ለክልል ምክር ቤት አባልነት የተመረጡትን ጨምሮ በዉስጡ ከተቀቀፉት የወረዳ ምክር ቤቶች በልዩ ሁኔታ የሚመረጡ አባላት ያሉት ሆኖ ይቋቋማል።ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

2. በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ለፌደራሉ የሕዝብ ተወካዮችና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት ደግሞ ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የብሔረሰብ ምክር ቤቶች የየብሔረሰባቸው የበላይ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ሥር የሠፈረው አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ የብሔረሰብ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ሲሆን የሚከተሉት ልዩ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ/ ብሔረሰቡ የሚጠቀምበትን የሥራ ቋንቋ መወሰን፣

ለ/ ብሔረሰቡ በቋንቋው ለመናገርና ለመጻፍ፣ ቋንቋውን ለማሳደግ፣ ለመጠበቅ፣ ለመግለጽ፣ ለማዳበርና ለማስፋፋት፣ እንዲሁም ታሪኩን በመንከባከብ ያለውን መብት ማስከበር፣

ሐ/ በዚህ ሕገ-መንግሥት ውስጥ ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጠው የሕግ አውጭነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በተደራጀበት አካባቢ ከክልሉ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር በማይጻረር ሁኔታ የራሱን ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎች አውጥቶ በሥራ ላይ ማዋል፣

መ/ የክልሉ ምክር ቤት ያጸደቀውን ብሔራዊ ክልላዊ ዕቅድና በጀት መሠረት በማድረግ የአካባቢውን ዕቅድና በጀት ማዘጋጀትና መርምሮ ማጽደቅ፣

ሠ/ የብሔረሰብ አስተዳደሩን አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤውንና ዋና አስተዳዳሪውን በምርጫ መሰየም፣

ረ/ በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርቡለትን የብሔረሰብ አስተዳደሩን ምክትል አስተዳዳሪና ሌሎች የአስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት መርምሮ ማጽደቅ፣

ሰ/ በብሔረሰብ አስተዳደሩ ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች ዳኞች ሹመት ረገድ የበኩሉን አስተያየት ለክልሉ ምክር ቤት መስጠት፣

ሸ/ የብሔረሰብ አስተዳደሩን ዋና አስተዳዳሪ ወይም ሌሎች የአስተዳደሩን ባለሥልጣናት በጥያቄ መጥራትና የአስፈጻሚውን አካል አሠራር መመርመር፣

# አንቀጽ 77

## ስለብሔረሰብ ምክር ቤት አመራር

1. የብሔረሰብ ምክር ቤት የራሱ ጽ/ቤት ኖሮት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በሚመረጡ የራሱ አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ ይመራል።ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

2. አፈ-ጉባኤውንና ምክትል አፈ-ጉባኤውን ዝርዝር ሥልጣንና ኃላፊነቶች አስመልክቶ በዚህ ሕገ-መንግሥት ለክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ የተጻፉት ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

3. ምክር ቤቱ ስራውን እንደአስፈላጊነቱ ራሱን በልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎች ያደራጃል።

# አንቀጽ 78

## የብሔረሰብ ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የብሔረሰብ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል።የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።

2. የብሔረሰብ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል።

3. ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ከሁለት ሶስተኛው በላይ የሚሆኑ በስብሰባው ላይ ከተገኙ የስብሰባው ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። የምክር ቤቱ ውሳኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል።

4. የብሔረሰብ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል።ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ-ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።የብሔረሰብ አስተዳደሩ ዋና አስተዳዳሪ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አንድ ሶስተኛው የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ-ጉባኤው ምክር ቤቱን ሰብስቦ የመጥራት ግዴታ አለበት።

# አንቀጽ 79

## ስለብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት

1. የብሔረሰብ አስተዳደር ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለሚመለከተዉ ብሔረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪና ለብሔረሰቡ ምክር ቤት ነዉ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና ለርዕሰ መስተዳድሩ ተጨማሪ ተጠሪነት ይኖርበታል፡፡

3. የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት የብሔረሰብ አስተዳደሩ ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪና ከአስተዳደሩ ዉስጥ የሚገኙ አስፈጻሚ መምሪያ ኃላፊዎች የሚካተቱበት አካል ሆኖ ይቋቋማል፡፡

# አንቀጽ 80

## የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ/ በብሔረሰብ ምክር ቤቱ በክልሉ ምክር ቤትና በፌደራሉ መንግሥት አካላት የወጡ ሕጎችና የተሰጡ ዉሳኔዎች በአስተዳደሩ ዉስጥ በሥራ መተርጎማቸዉን ያረጋግጣል፣

ለ/ የአስተዳደር ምክር ቤቱ አባላት የሆኑ መምሪያዎችንና ሌሎች አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ይወስናል፣ ሥራቸዉን ይከታተላል፣ በበላይነት ይመራል፣

ሐ/ የአስተዳደሩን ዓመታዊ በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፣ ለብሔረሰብ ምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲዉል ያደርጋል፣

መ/ የአስተዳደሩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በዝርዝር ይነድፋል፣ በብሔረሰብ ምክር ቤቱ ያፀድቃል፣ የተፈቀደዉንም ያስፈጽማል፣

ሠ/ በብሔረሰብ አስተዳደሩ ዉስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩንና የሕዝቡ ሠላምና ጸጥታ መጠበቁን ያረጋግጣል፣

ረ/ በብሔረሰብ ምክር ቤቱና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

2. የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ተግባራቸው በጋራ ለሚሰጡት ውሣኔና ለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀጽ 81

### የብሔረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ አሿሿምና የሥራ ዘመን

1. የብሔረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ በብሔረሰብ ም/ቤት ውስጥ አብላጫ መቀመጫ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት/ቶች/አቅራቢነት ከብሔረሰብ ም/ቤቱ አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል።

2. በዚህ ሕገ-መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የዋና አስተዳዳሪው የሥራ ዘመን የብሔረሰብ ም/ቤቱ የሥራ ዘመን ነው።

## አንቀጽ 82

### የዋና አስተዳዳሪው ሥልጣንና ተግባር

1. የብሔረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ የአስተዳደሩ ሥራ መሪ፣ የአስተዳደር ምክር ቤቱ ሰብሳቢና የብሔረሰብ አካባቢው ተጠሪ ነው።

2. ዋና አስተዳዳሪው ተጠሪነቱ ለብሔረሰቡ ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ነው።

3. ሌሎች የዋና አስተዳዳሪውን ሥልጣንና ተግባራት በሚመለከት በዚህ ሕገ መንግሥት የርዕሰ መስተዳድሩን ሥልጣንና ተግባራት አስመልክቶ የተደነገጉ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 83

### የብሔረሰብ አስተዳደር ምክትል አስተዳዳሪ

1. የብሔረሰብ አስተዳደር ምክትል አስተዳዳሪ በዋና አስተዳዳሪው አቅራቢነት ከመካከል በብሔረሰብ የሚሰየም ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

   ሀ/ በዋና አስተዳዳሪውና በብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

   ለ/ ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤

2. ምክትል አስተዳዳሪው ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪውና ለብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ነው።

## አንቀጽ 84

### የዋና አስተዳዳሪው ጽ/ቤት

1. የብሔረሰብ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል።
2. የዋና አስተዳዳሪው ጽ/ቤት የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤት ጽ/ቤት በመሆን ሊያገለግል ይችላል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

# ምዕራፍ አሥር

## ስለወረዳ አስተዳደር አደረጃጀትና ሥልጣን

### አንቀጽ 85

### አደረጃጀት

የወረዳ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት የሥልጣን አካላት ይኖሩታል።

1. በሕግ ከተደነገጉ ቀበሌዎች በሚወከሉ የሕዝብ ተወካዮች ተዋቅሮ የሚቋቋም የወረዳ ምክር ቤት፤

2. እነዚሁ ምክር ቤት አባላት መካከል ተመርጦ በሚሰየም የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አማካኝነት፣ የሚቋቋም የአስተዳደር ም/ቤትና፣

3. በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የተቋቋመ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል፣

## አንቀጽ 86

## የወረዳ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳ አስተዳደር በተደራጀበት አካባቢ የኢኮኖሚያዊ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ዕቅዶችን ለማዘጋጀትና ለመወሰንም ሆነ የክልሉ መንግሥት እንዲሁም የዞኑ ወይም የልዩ ወረዳ አካላት በየጊዜው የሚያወጧቸውን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ማናቸውም ሥልጣን ይኖረዋል።

2. እያንዳንዱ ወረዳ እራሱን የማስተዳደር፣ አካባቢውን የማልማትና በዉስጣዊ ጉዳዮቹ ላይ ዉሳኔ የመስጠት መብትና ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የዞን አስተዳደር የበታች አካል ነዉ።

## አንቀጽ 87

## ስለወረዳ ምክር ቤት አባላት አመራረጥና ተጠሪነት

1. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ወረዳዉ የተደራጀበት አካባቢ ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በሕዝብ ይመረጣሉ።

2. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸዉ ሕዝብ ይሆናል።

## አንቀጽ 88

## የወረዳ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳ ምክር ቤት በተቋቋመበት ወረዳ ዉስጥ ከፍተኛዉ መንግሥታዊ የሥልጣን አካል ነዉ። ተጠሪነቱም ለዞኑ ምክር ቤት ይሆናል።

አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

የወረዳዉን ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶችንና አስተዳደራዊ የሥራ ዕቅዶች፣ፕሮግራሞችንና በጀት ረቂቅ መርምሮ ያጸድቃል፤ በጀቱ በተመጣጣኝ ለቀበሌዎች ይመደባል።

በወረዳዉ ዉስጥ መሠረታዊ የግብርና የልማት ሥራዎች ወቅቱን ጠብቀዉ መካሄዳቸዉንና የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ የደንና እንክብካቤ ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ መከናወኑን ይከታተላል።

ነዋሪዉ ሕዝብ ለልማት ሥራ በስፋት የሚሳተፍበትንና የሚንቀሳቀስበትን አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል።

ዝርዝሩ በሕግ የሚወሰን ሆኖ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አፈ ጉባኤን፣ ምክትል አፈ ጉባኤውንና ዋና አስተዳዳሪውን በምርጫ ይሰይማል፤ በዋና አስተዳዳሪው የሚቀርቡለትን ምክትል አስተዳዳሪና ሌሎች የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት መርምሮ ያጸድቃል።

የራሱን ዉስጣዊ የአሠራር ሥነ ሥርዓት ደንብና መመሪያ ያወጣል።

ዝርዝሩ በሕግ የሚወሰን ሆኖ የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ፣ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብርና ሌሎች ግብሮች ወቅቱን ጠብቀዉ መሰብሰባቸዉን ያረጋግጣል፤ ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎችን ይጥላል።

ከክልሉ ከሚመደበዉና ከሚያስተዳድረዉ ዉጭ ያለዉንና የወረዳዉን የገቢ ምንጭ ይጠቀማል።

የፌዴራሉና የክልሉ ሕገ መንግሥታትና ሌሎች ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነዉ የወረዳዉን ሠላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ የሚያስችል ዝርዝር መመሪያ አዉጥቶ በሥራ ላይ ያዉላል።

የወረዳዉን ዋና አስተዳዳሪ ጨምሮ ሌሎች የወረዳዉን ባለሥልጣናት ለጥያቄ ይጠራል፤ የአስፈጻሚዉን አካል አሠራር ይመረምራል።

## አንቀጽ 89

## ስለ ምክር ቤቱ አመራርና አፈ ጉባኤ

1. የወረዳ ምክር ቤት የራሱ ጽ/ቤት እንዲኖረው ሆኖ ከአባላቱ መካከል ተመርጦ በሚሰየሙ አፈ ጉባኤ እና ምክትል አፈ ጉባኤ ይመራል፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

2. አፈ ጉባኤው ተጠሪነቱ ለወረዳው ምክር ቤት ሆኖ ወቅቱን ጠብቆ ምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራትና ጉባኤውን የመምራት ኃላፊነት ይኖርበታል፤

3. ሌሎች የአፈ ጉባኤው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች የክልል ምክር ቤቱን አፈ ጉባኤ አስመልክቶ በዚህ ሕገ መንግሥት የተደነገጉት እንደአግባብነቱ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 90

## የወረዳ ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ

ምክትል አፈ ጉባኤው ተጠሪነቱ ለአፈ ጉባኤና ለወረዳው ምክር ቤት ሆኖ፤

1. በአፈ ጉባኤው ተለይቶ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

2. አፈ ጉባኤው በማይኖርበት ጊዜ ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።

## አንቀጽ 91

## የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የወረዳ ምክር ቤት በየሶስት ወሩ ይሰበሰባል፤

2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። የምክር ቤቱ ውሳኔ በስብሰባ ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይተላለፋል፤

3. የወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞዉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በ15 ቀናት ጊዜ ዉስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራዉን ይጀምራል።

4. የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ በግልፅ ይካሄዳል። ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደርግበት ወቅት አፈ ጉባኤዉ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። የወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈ ጉባኤዉ የምክር ቤቱ አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።

## አንቀጽ 92

## ስለ ወረዳዉ አስተዳደር ምክር ቤት

1. የወረዳዉ አስተዳደር ምክር ቤት የተቋቋመበት ወረዳ ከፍተኛ የሕግ አስፈፃሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪና ለወረዳዉ ምክር ቤት ነዉ፣

2. የወረዳዉ አስተዳደር ምክር ቤት የወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪ እንዲሁም በወረዳዉ ዉስጥ የተቋቋሙ ዋና ዋና ዓላማ አስፈፃሚ ተቋማት ጽ/ቤት ኃላፊዎች የሚገኙበት አካል ሲሆን ከወረዳዉ ምክር ቤት በተጨማሪ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ተጠሪነት ይኖረዋል።

## አንቀጽ 93

## ስለወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

   ሀ/ የፌዴራሉና የክልሉ መንግሥታት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች ደንቦች፣ መመሪያዎች እቅዶችና ፕሮግራሞች በተቋቋመበት ወረዳ ዉስጥ በሥራ ላይ እንዲዉሉ ያደርጋል፤

ለ/ በወረዳዉ ዉስጥ የሚገኙ አስፈፃሚ አካላት በዕቅዳቸዉ ያስተባብራል፣ ሥራቸዉን ይከታተላል፣ ይመራል፤

ሐ/ በሕግ መሠረት የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ፣ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር እና ሌሎች ገቢዎችን ይሰበስባል፤ ተጨማሪ ገቢዎች ስለሚገኙበት ሁኔታ አጥንቶ ለወረዳዉ ምክር ቤት ለዉሳኔ ያቀርባል፡፡

መ/ የወረዳዉ ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ለወረዳዉ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲዉል ያደርጋል፤

ሠ/ የወረዳዉ ሠላምና ፀጥታ ይጠብቃል፤ የወረዳዉን የፀጥታና የፖሊስ አካላት ይመራል፣ ሥራቸዉን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

ረ/ የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ እቅዶችን አዘጋጅቶ ለወረዳዉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል፡፡ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ሰ/ ሕዝቡን ለልማት ሥራ በስፋት ያንቀሳቅሳል፣ የኅብር ልማትን ያፋጥናል፣ የተፈጥሮ ሀብትን ይጠብቃል፣ ያለማል፣ ይንከባከባል፤

ሸ/ በወረዳ ዉስጥ የሚገኝ ማንኛዉም ቅርስ ቅርስ አስፈላጊዉ ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገለት ስለመሆኑ በቅርበት ይከታተላል፤

ቀ/ በወረዳዉ ምክር ቤትና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል፤

2. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በመንግሥታዊ ሥልጣናቸዉ ለሚፈጽሙት ተግባርና ለሚያሳልፉት ዉሳኔ በጋራ ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡

## አንቀጽ 94

## ስለ ወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ አሰያየምና

## የሥራ ዘመን

1. የወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ በወረዳ ምክር ቤት ምርጫ አሸናፊ በሆነዉና በምክር ቤቱ ዉስጥ አብላጫ መቀመጫ ባገኘዉ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በምርጫ ይሰየማል፤

2. በዚህ ሕገ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን የወረዳዉ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል፤

## አንቀጽ 95
## የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለወረዳዉ ምክር ቤትና ለዞኑ አስተዳደር ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ የተሾመበት ወረዳ ተጠሪ፣ የአስተዳደሩ የሥራ ኃላፊና የአስተዳደር ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ነዉ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሰፈረዉ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪዉ፣

   ሀ/ የወረዳዉን አስተዳደር ይወክላል፤

   ለ/ የወረዳዉን አስተዳደር ምክር ቤት ይሰበስባል፣ ይመራል፤

   ሐ/ የፌደራሉና የክልሉ ሕገ መንግሥታት፣ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ፕሮግራሞች በወረዳዉ ዉስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸዉን ያረጋግጣል፤

   መ/ ምክትል አስተዳዳሪዉን ጨምሮ የወረዳዉን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት ለወረዳዉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፡፡ ምክትል አስተዳዳሪዉ የምክር ቤት አባል መሆን አለበት፡፡

   ሠ/ የወረዳ አስተዳደሩን ልዩልዩ ተቋማትና ቢሮዎች የሚያገናኙትን ቀበሌዎች ሥራ በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል

   ረ/ የወረዳዉ ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ የኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮግራሞች እና እቅዶች በቅድሚያ ጠብቀዉ መዘጋጀታቸዉን ይቆጣጠራል፣ ተግባራዊነታቸዉንም ይከታተላል፤

   ሰ/ የወረዳዉ ነዋሪ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ይጠበቅ ዘንድ ሕግና ሥርዓትን እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የሚሊሻና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ኸ/ ለወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት፣ ለወረዳው ምክር ቤትና ለበላይ የአስተዳደር አካላት በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፣

ወ/ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳዳሪው የወረዳውን ምክር ቤት ምሥራች ጉባኤ ይመራል፤

ዘ/ በወረዳው ምክር ቤትና በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 96

## የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ, ሥልጣንና ተግባር እና የሥራ ዘመን

የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ በወረዳው ዋና አስተዳዳሪ አቅራቢነት ከመካከሉ በወረዳው ምክር ቤት የሚሰየም ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. በዋና አስተዳዳሪውና በወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

2. ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

3. ምክትል አስተዳዳሪው ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪና ለአስተዳደር ምክር ቤቱ ነው።

4. የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን የወረዳው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

## አንቀጽ 97

## የዋና አስተዳዳሪው ጽ/ቤት

1. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪው የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል፤

2. የዋና አስተዳዳሪው ጽ/ቤት የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት ጽ/ቤት በመሆን ጭምር ሊያገለግል ይችላል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

## ስለ ቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀትና ሥልጣን

### አንቀጽ 98

### አደረጃጀትና ተጠሪነት

1. የቀበሌ አስተዳደር የክልሉ የመጨረሻ መንግሥታዊ የአስተዳደር እርከን ሲሆን በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት ተጠሪነቱ እንደየሁኔታው ለሚቀርበው የከተማና ወይም የወረዳ አስተዳደር ነው፡፡

2. የቀበሌ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል፡፡
   - ሀ/ የቀበሌ ምክር ቤት፣
   - ለ/ የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤትና
   - ሐ/ የማኅበራዊ ፍርድ ቤት፣

### አንቀጽ 99

### ስለቀበሌ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

1. የቀበሌ አስተዳደር በተደራጀበት አካባቢ የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕቅዶችን የማውጣትና መመሪያዎችን የማዘጋጀት፣ በሥራ ላይ የማዋልና እንዲሁም የመገምገም ሥልጣን አለው፡፡

2. እያንዳንዱ የቀበሌ አስተዳደር ራሱን የማስተዳደር፣ አካባቢውን የማልማትና በውስጣዊ ጉዳዮቹ ላይ ውሳኔ የመስጠት መብትና ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

### አንቀጽ 100

### ስለቀበሌ ምክር ቤት

1. የቀበሌ ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ሆኖ ተቋቁሟል፡፡

2. የቀበሌ ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ የሚመረጡ ይሆናሉ።

3. የምክር ቤቱ አባላት ተጠሪነት ለመረጣቸው ሕዝብ ነው፤

4. የቀበሌ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለወረዳ ምክር ቤት ይሆናል።

## አንቀጽ 101
## የቀበሌ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 100 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የወረዳው ምክር ቤትና የወረዳው ምክር ቤት በየጊዜው የሚያወጣቸው ሕጎችና መመሪያዎች በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

2. የበላይ የሀገሪቱ የአስተዳደር አካላት ከሚያወጧቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች መመሪያዎች ጋር በማይቃረን መንገድ የአካባቢ ማኅበራዊ ጉዳይ መመሪያዎችን አውጥቶ በቀበሌ ውስጥ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

3. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የቀበሌውን ሊቀ ጉባኤ፣ ምክትል ሊቀ ጉባኤና አስተዳዳሪ በምርጫ ይሰይማል፤ የቀበሌውን የአስተዳደር ምክር ቤት ያደራጃል፤

4. የነዋሪውን ሕዝብ ትችትና አስተያየት መሠረት በማድረግ በቀበሌ አስተዳዳሪ ተመርጠው የሚቀርቡለትን የማኅበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ይሾማል።

5. የበላይ በሆኑ የአስተዳደር አካላት የሚሰጡትን የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ፣ ልማትና አስተዳደራዊ ዕቅዶችና ፕሮግራሞችን ተቀብሎ በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ የሚውሉበትን ዝርዝር የሥራ አፈፃፀም መርሃ ግብር ያወጣል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

6. በሚመለከተው ቀበሌ ነዋሪ ሕዝብ የሚጠቀሙ ሌሎች ተጨማሪ ዕቅዶችን ያወጣል፤ ተግባራዊነታቸውንም በቅርበት ይከታተላል፤

7. የቀበሌዉን ነዋሪ ሕዝብ ለልማት ሥራ ያሰማራል፣ የተፈጥሮ ሀብትን ልማትና እንክብካቤ ሥራ በቅርበት ይከታተላል፣

8. የቀበሌዉ ነዋሪ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት መጠበቁንና ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፣

9. የቀበሌዉን አስተዳዳሪ ምክትል አስተዳዳሪ ለጥያቄ ይጠራል፣ የአስፈጻሚዉን አካል አሠራር ይመረምራል።

## አንቀጽ 102

## ስለ ቀበሌ ምክር ቤት አመራር

1. የቀበሌ ምክር ቤት የራሱ ጽ/ቤት የሚኖረዉ ሆኖ ከአባላቱ መካከል የሚመረጡ አንድ አፈ ጉባኤ እና አንድ ምክትል አፈ ጉባኤ ይኖሩታል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

2. አፈ ጉባኤዉ ተጠሪነቱ ለቀበሌዉ ምክር ቤት ሆኖ ምክር ቤቱን በወቅቱ ይሰበስባል፣ ይመራል፣ አጀንዳዎችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ቃለ ጉባኤዎች መያዛቸዉንና ዉሳኔዎች መጠበቃቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

3. ምክትል አፈ ጉባኤዉ ተጠሪነቱ ለአፈ ጉባኤዉና ለምክር ቤቱ ሆኖ፡-

ሀ/ በአፈ ጉባኤዉ ተለይተዉ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናዉናል፣

ለ/ አፈ ጉባኤዉ በማይገኝበት ወይም ሥራን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሰራል።

## አንቀጽ 103

## የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የቀበሌዉ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባዉን በወር አንድ ጊዜ ያካሂዳል።

2. ከምክር ቤት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። የምክር ቤቱ ዉሳኔ በስብሰባዉ ላይ በተገኙት የምክር ቤት አባላት የአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል።

3. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡ የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል፡፡ የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፡፡

4. የቀበሌው ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል፡፡ ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማይደረግበት ወቅት አፈ ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡ የቀበሌ አስተዳዳሪ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈ ጉባኤው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 104

## ስለቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት

1. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት የቀበሌው አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪና በቀበሌው ምክር ቤት አማካኝነት በተጨማሪ ተመርጠው የሚሰየሙ ሆነው በቀበሌው ውስጥ ከሚገኙ የማኅበራዊ አገልግሎት ሰጪ የመንግሥት ተቋማት ሠራተኞች በአባልነት የሚገኙበትና የበላይ በሆኑት የአስተዳደር አካላት የሚወጡ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የመጨረሻ አስፈጻሚ አካል ነው፡፡

2. የቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌ አስተዳዳሪ፣ ለመረጠው የቀበሌ ምክር ቤትና እንደሁኔታው ቀበሌ ለተቋቋመበት ከተማ አስተዳደርና ወይም ለወረዳው አስተዳደር ይሆናል፡፡

3. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በግልና በወል የቀበሌውን አስተዳደር ሥራ ይመራሉ፣ ያስተባብራሉ፡፡

4. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በሥራ ኃላፊነታቸው ለሚያጋጥማቸው ወጪና ለሚፈጽሙት ተግባር የሥራ የበጎ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 105

## የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 104 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረዉ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱትን ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ሀ/ የቀበሌዉ ምክር ቤት የሚያከናውናቸውን የልማት እቅዶችና ፕሮግራሞች በቀበሌዉ ዉስጥ በሥራ ላይ ያዉላል፤ የራሱን ዝርዝር የልማት እቅዶች ያዘጋጃል፤ ለቀበሌዉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፡፡

ለ/ በቀበሌዉ ዉስጥ የሚካሄዱ የማህበራዊ አገልግሎት እቅዶች በሥራ ላይ መዋላቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

ሐ/ የገጠር ልማትን ያፋጥናል፤ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ እንክብካቤና ልማት ሥራ በከፍተኛ ደረጃ እንዲካሄድ ያደርጋል፤ ሕዝቡን ለልማት ሥራ ያነሳሳል፣ ያስተባብራል፡፡

መ/ የቀበሌዉ ሠላምና ፀጥታ እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡

ሠ/ በአካባቢዉ ለሚገኙ ቅርስና ቅርሶች ተገቢዉን ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋል፤ በጥቅም ላይ ስለሚዉሉበት መንገድም የበላይ ለሆነዉ አካል ሃሳብ ያቀርባል፡፡

ረ/ የሥራ እንቅስቃሴዉን በሚመለከት ለቀበሌዉ ምክር ቤት በየወቅቱ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

ሰ/ በቀበሌ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል፡፡

2. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ዝርዝር የሥራ እቅዶቹን የሚያከናዉኑና ኃላፊዎቻቸዉን የሚከታተለዉም ሆነ የሚገመግመዉ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜዉ እየተገናኘ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 106

## ስለ ቀበሌ አስተዳዳሪ አስፈፃሚና የሥራ ዘመን

1. የቀበሌ አስተዳዳሪ በቀበሌ ምክር ቤት የምርጫ አሸናፊ በሆነዉና በምክር ቤቱ ዉስጥ አብላጫ መቀመጫ ባገኘዉ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ተመርጦ ይሰየማል፡፡

2. በዚህ ሕግ መንግሥት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የቀበሌ አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

## አንቀጽ 107

## የቀበሌ አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የቀበሌው አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌው ምክር ቤትና እንደሁኔታው ቀበሌው ለታቀፈበት ከተማና ወይም ወረዳ አስተዳደር ሆኖ የቀበሌው ተጠሪ፣ የአስተዳዳሪ ሥራ መሪና የአስተዳደር ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ነው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌው አስተዳዳሪ በዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ/ የቀበሌውን የአስተዳደር ምክር ቤት ይሰበስባል፣ ይመራል፣

ለ/ የበላይ በሆኑት የአስተዳደር አካላት የሚወጡትን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችንና አቅዶች ተቀብሎ በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሐ/ ምክትል አስተዳዳሪውን ጨምሮ የቀበሌውን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት ለቀበሌ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፤

መ/ የነዋሪውን ሕዝብ አስተያየት መሠረት አድርጎ በቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤት አማካኝነት እንዲጣራ ካደረገ በኋላ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ዝርዝር ለቀበሌ ምክር ቤት አቅርቦ ያሾማል።

ሠ/ ለቀበሌው ምክር ቤት፣ ለነዋሪው ሕዝብ እንደአስፈላጊነቱ ቀበሌ ለታቀፈበት ከተማና ወይም ወረዳ አስተዳደር በየጊዜው የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፤

ረ/ በቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤት፣ በቀበሌው ምክር ቤትና እንደሁኔታው በሚመለከተው ከተማና ወይም ወረዳ አስተዳደር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 108
## የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር የሥራ ዘመን

የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ በቀበሌው አስተዳዳሪ ተመርጦ ሹመቱ በቀበሌው ምክር ቤት የሚጸድቅ ሆኖ፣

1. በቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤት እና በአስተዳዳሪው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣

2. የቀበሌው አስተዳዳሪ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣

3. የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለቀበሌው አስተዳዳሪና ለአስተዳደር ምክር ቤቱ ነው።

4. የቀበሌው ምክትል አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

## አንቀጽ 109
## ስለቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት

የቀበሌ አስተዳደር የራሱ ጽ/ቤት ይኖረዋል።

ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 110
## የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት

1. የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የቀበሌው ማህበራዊ የዳኝነት አካል ሆኖ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

2. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀጽ 4 ሥር በተደነገገው መሠረት ተመርጠው የሚሾሙ ይሆናል።

3. የማኅበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የሥራ ዘመን የቀበሌ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል። ዝርዝሩ በህግ ይደነገጋል።

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት
## የክልሉ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች

### አንቀጽ 111
### ዓላማዎች

1. ማንኛውም የመንግሥት አካል የፌዴራሉንና የክልሉን ሕገ መንግሥታት፣ ሌሎች ሕጎችና ፖሊሲዎች በሥራ ላይ ሲያውል በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት መርሆዎችና ዓላማዎች ላይ መመስረት አለበት።

2. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ " መንግሥት " ማለት የጋምቤላ ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ማለት ነው።

### አንቀጽ 112
### የፖለቲካ ነክ ዓላማዎች

1. የክልሉን የፈጣን የልማት ራዕይ እዉን ለማድረግ ከሙስና የፀዳ፣ ቀልጣፋ፣ ዉጤታማ፣ ግልጽነት የተላበሰና ለሕዝብ ተጠያቂ የሆነ መልካም አስተዳደር ይመሰረታል። መንግሥት በዲሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሁሉም ደረጃዎች ራሳቸዉን በራሳቸዉ የሚያስተዳድሩበት ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።

2. መንግሥት በክልሉ ዉስጥ የሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነት የማክበርና የማስከበር እና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸዉ አብሮነትን፣ አንድነትንና ወንድማማችነትን ለማጠናከር ግዴታ አለበት።

### አንቀጽ 113
### የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች

1. የጋምቤላ ክልል ሥነ-ምኅዳር (በቂ ዝናብ ሰም መሬት) መሠረት ያደረገ፣ የክልሉን ተነጻጻሪ ብልጫዎች ላይ ያተኮረ፣ ፈጣን የተሳሰረና በገበያ የሚመራ የኢኮኖሚ

እንቅስቃሴ ያደርጋል። ስለሆነም የሕዝቡ፣ የባለሀብቶችና የራሱ የመንግሥት የልማት ኃይሎችን በቅንጅት ይመራል። ከአገሪቱ የገበያ ማዕከላት ለማገናኘት አቅም በፈቀደ መጠን የመሠረተ ልማት ዝርጋታን ያፋጥናል። መንግሥት ሁሉንም የክልሉ ነዋሪዎች ባላቸዉ እዉቀትና ሀብት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት።

2. የክልሉ ነዋሪዎች የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል አዲስ ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።

3. የተፈጥሮና ሰዉ ሠራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋዉ ሲደርስም ለተጎጂዉ ሕዝብ እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ አለበት።

4. መንግሥት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ስም በይዞታዉ ሥር በማድረግ ለሕዝቡ የጋራ ጥቅም እንዲዉል የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

5. የክልሉ የልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ሲዘጋጁ ሕዝቡ እንዲሳተፍ ማድረግ አለበት። የሕዝቡን የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት።

6. መንግሥት የሕዝቡን እዉቀት፣ ጉልበትና ሃብት በማቀናጀት ፈጣን ልማት የሚረጋገጥበትን መንገድ መቀየስ አለበት። ሕዝቡ በክልሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና እንዲኖረዉ ማድረግ አለበት። በተለይም ሕዝቡ ዕቅዶችና ፖሊሲዎችን በመደገፍ ብቻ ሳይሆን በማስፈፀምና በመገምገም መሳተፍ አለበት።

7. መንግሥት በኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት።

8. የመንግሥት ሠራተኛዉን ሕዝብ ጤንነት፣ ደህንነትና የሥራ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት።

## አንቀጽ 114
## ማህበራዊ ነክ ዓላማዎች

1. የአገሪቱና የክልሉ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና ማህበራዊ ዋስትና እንዲኖራቸው ያደርጋል።

2. ትምህርት ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከቶችና ከባህላዊ ተጽዕኖዎች ነፃ በሆነ መንገድ ይካሄዳል።

## አንቀጽ 115
## ባህል ነክ ዓላማዎች

1. የክልሉ መንግሥት መሠረታዊ መብቶችና ሰብዓዊ ክብርን እንዲሁም ዲሞክራሲንና ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑ ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት።

2. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግሥትና የሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች ግዴታ ነው።

3. የክልሉ መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነ ጥበባትን፣ ሳይንስንና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለበት።

4. የክልሉ መንግሥት ወጣቱን ትውልድ የመንከባከብ፣ በተሟላ ሥነ ምግባር የማነጽ፣ በአካልም ሆነ በአእምሮ ጠንክሮ ኃላፊነት የሚሸከም፣ ህዝቡን የሚወድና ለወገኑ የሚቆረቆር ዜጋና በራሱ የሚተማመን ዜጋ ሆኖ እንዲያድግ ያላሰለሰ ጥረት የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## አንቀጽ 116
## የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች

1. መንግሥት ሁሉም የክልሉ ነዋሪ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

2. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢውን ደህንነት የማያናጋ መሆን አለበት።

3. የሕዝብንና የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚመለከተውን ሕዝብ ሃሳቡን እንዲገልጽ መደረግ አለበት።

4. መንግሥትና የክልሉ ነዋሪዎች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው።

## ምዕራፍ አሥራ ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 117
## የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

1. በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ)ና በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2.17 በተደነገገው መሠረት ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 64 ንዑስ አንቀጽ 8 ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አውጥቶ ተግባራዊ ያደርጋል።

2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌውን አውጥቶ በሥራ ላይ ባዋለ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ አፈ ጉባኤው የክልሉን ምክር ቤት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ማሳወቅና የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌውን ለምክር ቤቱ በማቅረብ ማጸደቅ አለበት።

3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በክልሉ ምክር ቤት ተቀባይነት ካገኘ በሥራ ላይ ሊቆይ የሚችለው ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል። ሆኖም የክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲወስን የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው በየአራት ወሩ እንዲታደስ ለማድረግ ይችላል።

4. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና የክልሉ ምክር ቤት በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አማካኝነት የሚያወጧቸው ደንቦችና የሚወስዷቸው እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 1፣ አንቀጽ 16፣ አንቀጽ 17፣ አንቀጽ 19/1 እና /2/፣ አንቀጽ 22/1/፣ አንቀጽ 25/1/፣ አንቀጽ 26፣ አንቀጽ 29/1/ እና አንቀጽ 49/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ሥር የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸውም።

## አንቀጽ 118

## የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ

1. በክልሉ ውስጥ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በሚታወጅበት ወቅት የክልሉ ምክር ቤት ከአባላቱና በሕግ ባለሙያዎች መካከል የሚመርጣቸውና ሰባት አባላት ያሉት አስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ ማቋቋም ይችላል።
ቦርዱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው በክልል ምክር ቤት በሚጸድቅበት ጊዜ ይቋቋማል።

2. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

(ሀ) በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ምክንያት የታሰሩ ግለሰቦችን ስም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይፋ ማድረግና የታሰሩበትን ምክንያት መግለጽ፣

(ለ) በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈጻጸም የሚወሰዱት እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ ኢሰብአዊ አለመሆናቸውን መከታተልና መቆጣጠር፣

ሐ/ ማናቸውም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃ ኢሰብአዊ መሆኑን ሲያምንበት ርዕሰ መስተዳድሩ ወይም መስተዳድር ምክር ቤቱ እርምጃውን እንዲያስተካክል ሃሳብ መስጠት፣

መ/ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈጻጸም እርምጃዎች ኢሰብአዊ ድርጊት የፈጸሙ-ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ፣

ሠ/ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈጻጸም እንዲቀጥል ለክልሉ ምክር ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ያለውን አስተያየት ለምክር ቤቱ ማቅረብ፣

3. የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት ተልዕኮውን እንዳጠናቀቀ የሚፈርስ ይሆናል።

## <u>አንቀጽ 119</u>

## <u>የክልሉ ዋና ኦዲተርና ምክትሉ ዋና ኦዲተር</u>

1. የክልሉ ዋና ኦዲተርና ምክትሉ ዋና ኦዲተር በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ። ተጠሪነታቸውም ለክልሉ ምክር ቤት ይሆናል።

2. የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉ መንግሥት ተቋማትና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሂሳቦችን በመቆጣጠር በክልል ምክር ቤት የተመደበው ዓመታዊ በጀት ገንዘብ ዓመቱ ውስጥ እንዲሰራ ለተወሰኑት ሥራዎች በሚገባ መዋሉን ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።

3. የክልሉ ዋና ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል።

4. የዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 120
## የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሃሣብ ስለማመንጨት

የዚህ ሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሃሣብ፣

ሀ/ በክልል ምክር ቤት አባላት አንድ ሦስተኛ ሲደገፍ ወይም፣

ለ/ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ያብላጫ ሲደገፍ ወይም፣

ሐ/ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት የብሔረሰብ ዞንና የብሔረሰብ ልዩ ወረዳ ምክር ቤት በአንድ ሦስተኛዎቹ ሲደገፍ ወይም፣

መ/ በክልሉ ውስጥ የሚገኙት የወረዳ ምክር ቤቶች በአንድ ሦስተኛዎች ሲደገፍ ወይም፣

ሠ/ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት የቀበሌ ምክር ቤቶች በአንድ ሦስተኛው ሲደገፍ ሲወደድና ሲጠየቅ የሕገ መንግሥቱ መሻሻል ጉዳይ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ይቀርባል።

## አንቀጽ 121
## ሕገ መንግሥቱን ስለማሻሻል

1. የዚህ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ሁለትና ምዕራፍ ሦስት ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ሁለትና ሦስት ሲሻሻሉ ብቻ ነው። በዚህ መሠረት የሚደረገው ማሻሻያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ድንጋጌ መሠረት ይፀድቃል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ከተዘረዘሩት ውጪ ያሉት የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ብቻ ይሆናል።

ሀ/ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት የወረዳ ምክር ቤቶች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በአብላጫ ድምጽ ሲያፀድቁትና፤

ለ/ በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙት የብሔረሰብ ዞን ወይም የብሔረሰብ ልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በአብላጫ ድምጽ ሲያፀድቁትና፣

ሐ/ የክልሉ ምክር ቤት አባላት በሶስት አራተኛዉ ድምፅ ሲያፀድቁት ነዉ፡፡

3. ይህ ንዑስ አንቀጽና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት የቀረበዉን ማሻሻያ

ሀ/ በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙት የወረዳ ምክር ቤቶች ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲያፀድቁትና፣

ለ/ በክልሉ ዉስጥ ከሚገኙት የብሔረሰብ ዞን ወይም የብሔረሰብ ልዩ ወረዳ ምክር ቤቶች ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲያፀድቁትና፣

ሐ/ የክልሉ ምክር ቤት አባላት በሶስት አራተኛ ድምፅ ሲያፀድቁት ነዉ፡፡

## አንቀጽ 122
## ነባር ሕጎች ስለመፅናታቸዉ

በብሔራዊ ክልሉ ዉስጥ እስካሁን ድረስ ፀንተዉ የሚሰራባቸዉ ነባር ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተሻሽለዉ እስኪወጡ ከዚህ ሕገ መንግስት ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## አንቀጽ 123
## የመጨረሻ ሕጋዊ ሰነዱና ስለሰነዱ ቅጂ

የዚህ ሕገ መንግስት የአማርኛ ቅጂ የመጨረሻዉ ሕጋዊ ሰነድና ይፋዊ ሠነድ ነዉ፡፡